# የዕንባ ምንጭ

ከበልጅግ አሊ

beljig.ali@gmail.com

-፩-

እንግዳውና ቤተሰቡ ላይ የደረሰውን ችግር መስማት ጭንቀት ስለፈጠረብኝ ቀስ ብዬ ከጓደኛዬ ቤት ወጣሁ ። ቀዝቃዛ የሆነውን አየር እየተነፈስኩ ብቻዬን ወደ ቤቴ ተጓዝኩ ። የሰማሁት የፈጠረብኝ ሃዘን ሳላስበው ውስጤን ገልብጦ ፍሳሽ በፍሳሽ አደረገኝ ።በእንባዬ ውስጥ ከአዲስ አበባ የመጣው የጓደኛዬ ወንድም ይታየኛል ። ድሮ በቃሌ የማውቀውን የሎሬት ፀጋዬ ግጥም ለማምበብ ሞከርኩ፡ -

## ወንድ ልጅ ብቻውን ነው እሚያለቅስ

ከወዳጅ ከዘመድ እርቆ
አንጀቱን በአንጀቱ ታጥቆ
ተሸሽጎ ተገልሎ ፣ ተሸማቆ ተሸማቆ
ከቤተሰብ ተደብቆ
መሽቶ የማታ ማታ ነው ፣ሌት ነው የወንድ ልጅ እንባው
ብቻውን ነው የሚፈታው ። . . .
ብቻውን ነው የሚረታው። . . .

ግጥሙን ትቼ የቀኑን ውሎዬን ማሰብ ጀመርኩ ። . . .

አውሮፕላን ማረፊያው ከወትሮው በተለየ በመንገደኛ ብዛት ተጥለቅልቋል ።በሰሜን አፍሪካ የተነሣውን አመጽ በመሸሽ ወደ አገሩ የሚመለሰው አውሮፓዊ ቁጥር ከመብዛቱ የተነሣ በተለመደው በረራ ላይ ተጨማሪ አውሮፕላኖች ታዘዋል ። ጋዜጠኞች ከሊቢያ የሚመለሱትን መንገደኞች ስለ ሁኔታው ለመጠየቅ አሰፍስፈው ይጠብቃሉ ። እኔና ጓደኛዬ ከአዲስ አበባ የሚመጣውን ታላቅ ወንድሙን ለመጠበቅ በተጠንቀቅ ቆመናል ። በሊቢያ ይኖሩ የነበሩ የአውሮፓ ነጮች በድንጋጤ ቀይ አፈር መስለው ቁጥጥሩን አልፈው ይወጣሉ ። ቤተሰቦቻቸው ተሰብስበው በደስታ ይቀበሏቸዋል ። ጋዜጠኞቹም እየተራወጡ የተመለሱትን ተጓዦች ስለነበሩበት ሁኔታ ይጠይቃሉ ።

ምን እንደሚጠይቋቸው ለመስማት ጥረት አደረግሁ ። ባልሰማው ይሻለኝ ነበር ። ጋዜጠኞቹን በጣም ያሳሰባቸው ሊቢያ ውስጥ የሚያልቀው ሕዝብ ሳይሆን ከዋናው ከተማ ትሪፖሊ ራቅ ብለው የሚገኙ ጀርመኖች ጉዳይ ነበር ። ይህንን የማይረባ ግርግር ትቼ ወደ መጣንበት ጉዳይ ተመለስኩ ።የጓደኛዬን ታላቅ ወንድም ዘለግ ያለ ሰውነቱና ጠቆር ያለ መልኩ ከሌሎች ሁሉ ጎልቶ በሩቅ እንዲታይ አድርጎታል። ከተለመደው የጀርመኖች የዘረኝነት የተንዛዛ የቪዛ ቁጥጥር አልፎ ካለ አንዳች ችግር በቶሎ በመውጣቱ ተደሰትን ።

እኛን ሲመለከት ጎንበስ ብሎ መሬትን ሳም ሳም አደረገ። ተንበርክኮ ወደ ሰማይም አንጋጦ ለአምላኩ ምስጋና አደረሰ ። ምን ማድረጉ እንደሆነ ስላልገባን ዝም ብለን ተመለከትነው ። ወንድሙን አቅፎ ይሰማል ብለን ስንጠብቅ መሬቱን ሲስም ግራ ተጋባን ። አካባቢው ያሉት ፈረንጆች ምን እንደሆነ ስላልገባቸው አፍጠው ይመለከቱታል ።

ጋዜጠኞቹ ከሊቢያ የመጣ መስሏቸው እየተሯሯጡ ተጠጉት ። ጥያቄያቸውን አዥጎደጎዱት ።

"Können Sie Deutsch sprechen?" በጀርመኛ ጠየቁት ።መልስ ሲያጡ ደግሞ በእንግሊዘኛ ፡ -
"Can you speak English?"
"Can you tell us about Libya?"

"የሚጮኽለት አጥቶ ነው እንጂ የእኛም ሃገር ከሊቢያ ይብሳል" ብሎ ጮክ ብሎ በአማርኛ ነገራቸው ።ድፍረቱ ቢገርመኝም ሳቄ መጣ።ማን ሰምቶት ! ብሶቱን ተናገረ እንጂ አማርኛ እንደማይገባቸው አጥቶት አይመስለኝም። አውሮፓላን ማረፊውን ከበው ሰው ሲሸኙና ሲቀበሉ የሚውሉ ወያኔዎችና ደጋፊዎቻቸው ብዙ እንደሆኑ ስለምናውቅ እኔና ጓደኛዬ ሲመለስ ችግር ይገጥመዋል ብለን ደነገጥን ።

"where are you from?" አንዱ ጋዜጠኛ ጠየቀው።

"Ethopia!" ጮክ ብሎ መለሰ ።

ጋዜጠኞቹ ፍላጎታቸው በአንድ ጊዜ ሚሸሸ ። ጓደኛዬና እኔ ተያየኝን ።ሳንነጋገር ተግባባን ።እኛ ነዳጅ ቤንዚን የለን ! እኛ ሃብታም አይደለንም ! ለመሞትማ በ97 ምርጫ ከሁለት መቶ ሰው በላይ ያውም ወያኔ ያመነው ሞቶ አልነበር ። ሌላውን ቤት ይቁጠረው ። እስረኛውስ . . .

ጓደኛዬ ጋዜጠኞቹን ከመጤፍ ባለመቁጠር ወንድሙ እንደምንም ብሎ ከተንበረከከበት አነሳውና "ምን ሆንክ ?" ብሎ ጠየቀው።

"ምንም አልሆንኩም ደስታው ነው" ሲቃ እያኮላተፈው።

ይህንን ያህል መሬት የሚያስመው ነገር ምን እንደሆነ ሊገባን አልቻለም ። ይህንን አልጠበቅንም ነበር ። ይብዛም ይነስም ወንድሙ የአባትና የእናታቸውን ቤት ውስጥ እንደሚኖር ያውቃል ። ሥራም አለው ።ድንጋጤው ከሰውነቱ ላይ ሳይለቅ የውሸት ፈገግታ እያሳየ አርዕስቱን ቀየረው ፡ -

- "እንዴት ነበር ጉዞ ?" ።
- "ምንም እንቅልፍ ሳይወስደኝ እዚህ ደረስኩ ። ይመልሱኛል ብዬ በጣም ፈርቼ ነበር ። እግዜር ይስጠው ሰውዬው ምንም አላላኝም ። ፓስፖርቴን አይቶ ፈርሞበት ግባ አለኝ። ያን ሁሉ ስዘጋጅ ከርሜ ምንም ሳይጠይቀኝ አስገባኝ"።

ወንድምዬው ለምን መሬት እንደሳመ ገባው ። ተገረመ። ጥሩ የሚኖረው ወንድሙ እንዲህ የተደሰተ ምንም የሌለው ደሃ ቢመጣ ምን ያህል ይደሰት ይሆን ? ብሎ አሰበ ።ወንድሙ ኩሩ እንደሆነ ያውቃል ። ብዙ ችግርም በሕይወቱ ውስጥ እንዳሳለፈም ያስታውሳል ። የወንድሙ መለወጥ በጣም አሳሰበው ።ምን አዲስ ነገር ተፈጥሮ ይሆን እያለ እያንሰላሰለ ፡ ጉዞ ወደ ቤት ሆነ ፡፡

- "ቤተሰብ እንዴት ነው ?" ነበር የመጀመሪያው ጥያቄ ።
- "ደህና ናቸው በጣም ናፍቀውሃል ። እነሱማ ምን ይሆናሉ እድሜ ላንተ !

የተለመደው ጥየቄ ቀጠለ ።

- "ማዘርስ እንዴት ናት ተሻላት ወይ ?"
- " ደህና ነች ። ሰሞኑን ጠበል ከርማ መጣች"።
- " ሐኪም ቤት ለምን አትሄድም ?"
- "ሁሉንም ሞከረች እኮ ! እዛ ሃገር ምን ደህና ሐኪም አለና ነው ? ሁሉም የሚሮጡት ለገንዘብ ነው"።
- "ለመሆኑ እከሌ እንዴት ነው ?"
- "እሱማ ዛሬ የትና የት የደረሰ ሃብታም ነው ።ከሰዎቹ (ከወያኔ)ግንኙነት አለው ይባላል።"
- "እከሌስ ?"
- "አይ እሱማ በሽተኛ ሆኖ ? የሚታከምበት ገንዘብ አጥቶ እየተሰቃየ ነው ። የዘንድሮ ሕክምና መድሃኒት ለሃብታሞቹ ብቻ ነው።"
- "እከሊትስ ?"
- "ሦስት ልጅ ወለደች እኮ ።"
- "እከሌስ ?"
- "እሱ እኮ ወጥቷል ። የት እንደሆነ አላውቅም ።"
- "የእከሌ ወንድምስ ?"
- "እሱማ አረፈ እኮ ። አንድ ሰሞን ከስት ብሎ አይቸው ነበር ። በኋላ ማረፉን ሰማሁ ።"
- "የእከሌ እናትስ አባትስ?"
- "እነርሱማ በጣም አርጅተዋል ። አሁን በቅርብ ቀብር ላይ አይቻቸው ነበር ። "
- "ሠፈሩ እንዴት ነው ?"

- "በዚያ በኛ ሠፈር መንገድ እንሰራለን ብለው ቤቱን ሁሉ አፈራረሱት። ለሕዝቡ መልቀቂያ ግምት ብለው የሚያስቅ ትንሽ ገንዘብና ተለዋጭ  ቦታ ሰጥተው አሰናብተዋቸዋል ። ሌሎቹን ኮንደሚኒየም ግዙ እያሉ የማይችሉትን  ዕዳ ውስጥ እንዲገቡ እየገፋፉ ነው። ሠፈርተኛውን በተኑት ። ከልደታ ፊት ለፊት ያለውን ይዞ የድሮውን ናትናኤል ቡና ቤት ጨምሮ እስከላይ ድረስ ፈርሷል። ወያኔ በ97 ምርጫ ያቄመውን ቀስ ብሎ እየተበቀለ ነው። ትንሽ ይቆይ እንጂ "አሳዳሚ" ነች የሚላትን ልደታን ያፈርሳታል ይሆናል። ማን ከልክሎት !

- "የእኛስ ቤት እንዴት ሆነ ?"

ስለዚህ ቤት አሰራር ጓደኛዬ ሁል ጊዜ ይነግረኛል ። ሳጂን ሜጀር የነበሩት አባቱ በወታደር ደሞዝ መሬቱን ገዝተው ቤት እንደሠሩም እየተደነቀ ነግሮኛል ። ከኮሪያ ዘመቻም ያገኙት ተጨምሮ ነው ብሎ አጫውቶኛል ። ጓደኛዬ ለዛ ቤት ትልቅ ፍቅር አለው ። እሱም ወንድሙም እዛው ቤት ነው የተወለዱት ። አባትዬው ከጎን የሠሩት ሁለት ደጃፍ ቤት በደርግ ዘመን ሲወረስባቸው በንዴት በሽታ ላይ ወድቀው ሲሰቃዩ ከርመው እንደሞቱ አጫውቶኛል ። ስለ ቤቱ ጓደኛዬ ብቻ ሳይሆን እኔም ለመስማት ቸኮልኩ ።

- "ትደነግጣለህ ብለን አልነገርንህም እንጂ የእኛንም ቤት አፈረሱት ። ያ እናት አባታችን በወታደር ራሽን ቀለብ እየኖሩ  ከጉሮሮቻቸው ቆጥበው፣ ያ አባታችን ኮሪያ ዘምቶ ያገኘውን ጥሪት በመጠቀም ፣ ያ በኦጋዴን በርሃ ለሃገሩ ሲል እየደማ ለልጆቼ ይሆነኛል ብሎ የሠራውን ቤትና መሬት ይህ መንግሥት በጉልበት ወሰደብን ። የደርግ መንግሥት ያከራየው የነበረውን ሁለት ደጃፍ ቤት ነጥቆ በረሃብ አስቃይተው ገደሉት። የአሁኖቹ ደግሞ ቤቱን አፍርሰው እኛን አስወጡን ። እንቢ ካላችሁ እላያችሁ ላይ እናፈርሰዋለን ብለው ዛቱ ።

የጓደኛዬ ዓይኖቹ በእንባ ሲሞሉ ታየኝ ።

- "ሕዝቡ እንዲህ ግፍ ሲሠሩ ዝም ይላቸዋል እንዴ ?" ጣልቃ ገብቼ ጠየቅሁ ።

- "ሕዝብ ምን ያደርጋል ። የአዲስ አበባ ሕዝብ  ለእነርሱ ጠላታቸው ነው ። እንኳን ቤቱን ፣ ንብረቱን እኛንስ ቢገድሉን ማን ይጠይቃቸዋል ። በቅንጅት ጊዜ ያ ሁሉ ሰው አልቆ ማን ተናገራቸው ? በዛ ላይ ደግሞ በዘር ከፋፍለውት ! አንዱን እየጠቀሙ አንዱን ይጎዳሉ ። ግፍ ፣ የሠው እንባ የሚል ነገር የለም "።

- "የመሬትና የቤት ግምት አይሰጧችሁም እንዴ ?" የወንድሙ ጥያቄ ነበር ።

- "አዬ ግምት ! የቤቱን ግምት ብለው ይሰጡሃል ። መሬትማ የእነርሱ ነው ። በጦርነት አሸንፈው ያስገበሩት አይደለም ? ስትሸነፍ እኮ ንብረትህን ብቻ አይደለም የምታጣው ፣ ስብዕናህንም ነው ። ማን ከሰው ቆጥሮን ። አያታችን የሚነግረን ትዝ አይልህም ? በጣሊያን ጊዜ ፈረንጁ እንዲህ ያደርግ ነበር እያለ ። ከዚያ ጊዜ የአሁኑ ምንም አይተናነስም ። የሚሰጡት ገንዘብ እንኳ ሌላ ቤት ሊሠራ የመንፈቅም የቤት ኪራይ የማይሆን ነው ። ከኛ ሠፈር የለቀቁትን መብራት፣ውሃና ፣ መንገድ የሌለው ቦታ ሰጥተው አሰፈሩን። እነዚያ ሁሉ ሽማግሌ ጡረተኞች ከነቤተሰቦቻቸው ከኖሩበት፣ ከወለዱበት ፣ ከከበዱበት  ቦታ እየተነሱ አዲስ ቤት ምስረታ አዲስ አበባ ውስጥ ተሰደዱ ። የሚገርመው ደግሞ ደሞዝህ አዲስ ከሚሠጡህ ቦታ ሥራህ ድረስ ለትራንስፖርትም አይሆንም ። ወያኔ ደሃውን አንድ ቦታ እየሰበሰበ አሜሪካን አገር "ጌቶ" እንደሚሉት እየፈጠረ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ገሃነም እሳትና መንግሥተ ሰማያት አብረው ናቸው ።ብታየው ብሽቅጥቅጥ ያለ ኑሮ ነው"።

- "ልጆቹስ ትምህርታቸውስ?" ።

- "ደግሞ ዘንድሮ ስለ ልጅ ትምህርት ይታሰባል እንዴ ? በልቶ ካደረም ጥሩ ነው ። አዲሱ የሠጡን ቦታ ትምህርት ቤት የለም ። ሕክምናን ትረሳዋለህ ። መንገድ ፣ መብራት ፣ ውሃ ፣ ወደፊት የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ሲጠነክር ይገባል ተብለናል ። በዚህ አይነት ቤተሰቡንንና ልጆቼን ምን ላድርጋቸው ።ሰው መንፈስ አይደለም ። ሥጋውን ማሸነፍ አለበት ።(መብላት ፣መጠጣት ፣ መልበስ ፣ . . . ) ለሁሉም መሠረት የሆኑ ፍላጎቶች ማሟላት ይጠበቅበታል ። እነርሱ እኛ በመንፈስ እንድንኖር እነሱ ግን በዛች ሃገር እንዲደላቀቁ ነው የሚፈልጉት ። ምን እናድርግ እኛም ሥጋ ሆንና መኖርን ተመኘን ። እኔ በበኩሌ  ሁል ጊዜ እንደዚህ መኖር አልቻልኩም። ዛሬ አላስገባም ቢሉኝ ኖሮ ሕይወቴን አጠፋ ነበር ።  ሌላ ምንም ተሰፋ የለኝም ነበር ።ምን እሱ ብቻ ሌላም ብዙ ያልነገርኩህ አለ" ።

- "ደግሞ ምን ተፈጠረ ?" ራሱን ለማጥፋት ያሰደረሰውን ችግር ለመስማት በመቸኮል  ወንድምዬው ጠየቀ ።

-

-

- "ለሃያ አምስት አመት የሠራሁበት መሥሪያ ቤት ውስጥ እንዲዚሁ የእነርሱ ሰዎች ተሰባስበው የኢሕአደግ ድርጅቶች ውስጥ የሌሉበት በሙሉ ከያዝነው ቦታ እንድንወርድ ጠየቁን ። እኛም ባይሆን ድርጅቱ ውስጥ ታስገቡናላችሁ እንጂ እንዴት እንዲህ ይሆናል? ብለን አልን ። እሺ ግቡ ተባለና ተፈቀደልን። ሰባ አምስት በመቶው የመንግሥት ሠራተኛ ተገዶ የኢሕአደግ አባል ሆኗል " ።

- "የምን ድርጀት ? "
- "ቲ.ፒ ኤል. ኤፍ በየዘራችን ያቋቋመልን ውስጥ ነዋ ። ለምሳሌ እኔ አማራ ስለሆንኩ ብአዴን፣ ኦሮሞ የሆኑት ደግሞ OPDO ፣ ደቡብ ሕዝቦች ደግሞ እንደዚሁ በሚመለከታቸው የዘር ድርጅት ውስጥ ገባን ። እንደምታውቁት እነዚህ የዘር ድርጅቶች ተሰብስበው ነው ኢሕአዴግን የሚመሠርቱት ። ሁሉንም የሚቆጣጠራቸው ቲ.ፒ ኤል. ኤፍ ሆኖ ማለት ነው ።"
- " ከዛ በኋላ ሰላም አገኛችሁ ? "

- "እኛ ሕፃናት እናሳድጋለን ብለን ባርነቱን ለመቀበልና የማናምነውን ለመፈፀም እሺ ያልነውን ትንሽ ታገሱን ። ሌሎቹን ድርጅቱ አንገባም ያሉትን በቅያሪና በጡረታ ወዲያው አባረሯቸው ። እኛም ድርጅቱ ከገባን ምን ይፈልጋሉ ፣ጉዳዩ በዛ ተፈጽሟል ብለን ዝም ስንል ሲተበትቡ ከርመው ግምገማ የሚል ነገር አነሱ ። አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ይሉታል እንጂ ግምገማ ማለት በአንድ በኩል ታማኝ ያልሆኑትን ከሥልጣን በማንሳት ታማኝ የሆኑትን በቦታው ማስቀመጥ ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሠራተኛውን እርስ በእርሱ ማባላት ነው ። እንግዲህ እኛ ተገመገምንና በቂ ታማኝ ሆነን ስላልተገኘን ከያዝነው ቦታ ተነስተን በቦታችን ከሌሎች የዘር ድርጅቶቻቸውና በቲ .ፒ ኤል. ኤፍ የተመረጡ ቦታውን ያዙት ። ይህ እንግዲህ እርስ በእርሳችን ጦርነት እንድንጀምር ነው ።መቼም መምከር አይቀር ለበላይ አቤት ብለን ነበር ። መልሱ ክልላችሁ አማራ ስለሆነ ባሕር ዳር መሄድ ትችላላችሁ ተባልን ። አይ ሥራውን አትከልክሉን እንጂ ሥልጣን ገደል ይግባ ብለን ተቀበልነው ። የእኔን ቦታ አንድ ከትምህርት ቤት ገና የተመረቀ ወጣት ሰጥተውት ነበር ። ልጁ ደቡብ ሕዝቦች ድርጅት አባል በመሆኑ ነው እንጂ ምንም አያውቅም ፣ ልምድም አልነበረውም ። ሥራው እንደፈለጉ ያደርጉት ጀመር ። ሁሉም ነገር በሙስና ተበላሸ ። ያው እሱ ደግሞ ጊዜው ደርሶ ግምገማ ተብሎ ከሥልጣን ወረደ ። በእሱ ቦታ ሌላ ከኦሮሞ ድርጅት ተተካ ። እሱም ብዙ አልቆየ ተባረረና አሁን ትግሬዎቹ ራሳቸው ይዘውታል ። እንዲውም ከኦሮሞ ድርጅት ተመርጦ የነበረው በኋላ አንድ ገንዘብ የሚገኝበት ቦታ ተመድቦ ነበር ። ከዚያ ጠፍቶ እዚህ አውሮፓ ነው ይባላል ። "

- "ምን ይሠራል እዚህ ? "

- "በሙስና ተከሶ ሊታሰር ሲል አገር ጥሎ ጠፋ ። ነገሩ ሙስና ይበሉት እንጂ የበላውን ገንዘብ ለትግሬዎቹ አላካፍልም ብሎ ነው ይባላል"።

- "እሱ እንኳ ማን ያውቃል እዚህ ተጣላሁ ብሎ ይምጣ እንጂ ወያኔ ዲያስፖራውን እንዲከፋፍል ሥራ ሰጥቶት ይሆናል። ለመሆኑ በሙስና የተከሰሰ ሰው ሃገር ጥሎ እንዲወጣ ይፈቀድለታል እንዴ ?" ብዬ ጠየቅሁ ።

- " አልሰማችሁም እንዴ የሙስናውን አጣሪ ኮሚቴ በሙስና ትሸውደው የለም እንዴ ? ዋናው ሙስናው እኮ ያለው እዛው ነው ። የዓሣ ግማቱ ከአናቱ !"

- "እንዴት ? "

- "የሙስናው ኮሚቴ አንተን በሙስና ሲከስህ በከባድ አንቀጽ እንዳይከስህ በሙስና ትይዘዋለህ ። ይህ ማለት የዋስ መብት የሚጠብቅ አንቀጽ እንዲጠቅስ ማለት ነው ። ኮሚቴው ቀለል ያለ አንቀጽ ይጠቅስና ይከሰሃል ። ፍርድ ቤት ስትቀርብ ራቅ ያለ ቀጠሮ እንዲሰጥህ ደግሞ በዳኞቹ ላይ ሙስና ትሠራለህ ። በዛ ሰዓት ገንዘብህን ታሸሻለህ ፣ በየኤምባሲው ለቪዛ ሙስና መስራት ትጀምራለህ ። ለእንግሊዝና የአሜሪካ ቪዛ ከተወደደብህ የሌላው አውሮፓ ይረክስልሃል ። ከመቶ እስከ ሁለት መቶ ሽህ ብር ያስፈልግሃል። እሱ ትንሽ ጫን ያለ ገንዘብ ስለነበረው አሁን እንግሊዝ ነው ያለው አሉ ።"

- "የእሱን እንተወውና፣አንተን ከሥራህ አባረሩህ እንዴ ?" ወንድምዬው ቁርጡን ለማወቅ በመቸኮል ጠየቀው ።

- "ለመባረር አንድ ሃሙስ ነበር የቀረኝ። ትንሽ ይህ የሰሜን አፍሪካ አመጽ ተነስቶ በወያኔዎቹ ፍርሃት አለች መሰለኝ ሁኔታውን አራዝመውታል ። ለነገሩም ስለፈሩ ነው መሰለኝ ጥሩ ሰላምታም መስጠት ጀምረዋል ።

ትዕቢታቸውም ቀንሳለች ። ማን እነርሱን ያምናል ። የቅንጀት ጊዜም እንዲሁ ነበር ያደረጉት ። ቅንጅት ሲጠፋ ቂም ይዘው አሰቃዩን እንጂ ። የዛሬ አመት አካባቢ እነሱማ ወደ ክልላችን ባሕር ዳር ትሄዳላችሁ እያሉን ነበር ። በእሱ እየተጨነቅን ሳለን ቤቴን አፈረሱብኝ ። ቤቱ እንኳ ቢኖር ኖሮ እንኳ  ሌላ ሥራ ይፈለግ ነበር ። ለነገሩ ነው እንጂ  ያ ሃገር የሚኖርበት አልሆነም " ።

- "የእኛ ቤት የነበረበት ቦታ ታዲያ ምን ሆነ ?"

- "አጥረው አስቀምጠውታል ። በእኛ ቦታ ላይ አንድ ዴያስፖራ ቤት ሊሠራበት ነው አሉ ። መቼም ያንን የታጠረ ቦታ ስመለከት በቤንዝል አቃጥለው ነው የሚለኝ ። እኔና ልጆቼ የምንበላው ፣ የምንኖርበት እየተከለከልን ፣ ቤተሰባችን ሲፈርስ የፖለቲካ ችግር ሃገር ውስጥ አለብኝ ብሎ በአውሮፓና በአሜሪካ ፈቃድ ያገኘ ሁሉ የእኛ ቤት ለማፍረስ ፣ ልጆቻችንን ለማስራብ ፣ እንዲህ እንድንሠቃይ ሲያደርጉን እንደ ግብጽና እንደ ሊቢያ ለእኛም ቀን የማያልፍልን ይመስላቸው ይሆን? እኔስ አንተ ስላለህ እዚህ መጣሁ ገኛ ሠፈርን ፣ ዳርማርን ፣ እስቲ አስበው ያ ሁሉ ደሃ ምን ይደርስ ይሆን ? ሃገራችን እንዳልሆነ ፣  እትብታችን የተቀበረበት ፣ ተወልደን ያደግበት ምድር ፣  አንድ መኖሪያችንን ስንቀማ ቅኝ ግዛት አይደለም ይባላል ? ለመሆኑ ምርጫችን ምንድነው ? ከቤት አንወጣም ማለት ? በቡልዶዘር ከነልጆቻንን እዛው መቀበር ? የእነርሱ ልጆች በውጭ ሃገር ለትምህርት ሲላኩ የእኛ ልጆች ከቤታቸው ተባረው በላክስቲክ ቤት ውስጥ መንገድ ዳር ላይ መኖር ?  እነርሱ የመዋኛ ቦታ ያለው ቤት እየሰሩ የበጋውን ሙቀት በመዋኘት ሲከላከሉ፣ እኛ ጀሪካን ይዘን የምንጠጣው ውሃ ፍለጋ መዞር ? እኛ ሻማ ቆጥበን ስንኖር እነርሱ ጄኔሬተር ገዝተው 24 ሰዓት አሸሼ ገዳሜ ማለት ? እነርሱ ዘፈን ከፍተው ከበሮ ሲደልቁ ፤ እኛ ለሞተ ልጃችን የምናለቅሰው እንባ አጥተን መኳተጥ ? እነርሱ ሜርሴዲስ ፣ ሃመር ፣ ቢ.ኤም ፣ ደብሊዉ ሲመርጡ እኛ ጫማችን አልቆ ጠርሙስ እንግራችንን እያደማን መሰቃየት ፣ ይህ ከሊብያ፣ ከቱኒስ፣ ከግብጽስ አይብስም ?"

ስቅስቅ ብሎ ሲያለቅስ ተው እንጂ እንዲህ መሆን አያስፈልግም አልኩት ።

"ዋ ለምን ይሆን እንዲህ ሆድ የሚብሰኝ ። በሰው ፊት ጥንክር ያልኩ ብረት ነበርኩ ። ብዙ . . .  ብዙ . . .  መሸከም የምችል ። ብዙዎቹ የሚደነቁብኝ . . .  ባለመረታትና . . . በጽናት . . .። ይህ የተነፋ ጥንካሬዬን ያስተነፈሰው ጉዳይ ይገርመኛል ። ልጆቼ ከእኛ በተሻለ ኑሮ ይኖራሉ ብዬ ጣርኩ ። ጥሩ ትምህርት ፣ ጥሩ ምግብ ፣ጥሩ ልብስ  ቢያገኙ ብዬ ታገልኩ ። ጊዜ የሰጠው ጉልበተኛ እንደፈለገ ያደርገን ጀመር ። ከሥራ ፣ ከመኖሪያችን በፈለገው ሰዓትና በፈለገው ጊዜ ያፈናቅለናል ።

"ልጅህ ከቤት ወጥቶ የመንገድ አዳሪ ሲሆን ማየትን የመሰለ የቁም ሞት አለ ? ተከብረህ በኖርክበት ሰፈር ተዋርደህ ልጆችህ ወደ ልመና ሲሰማሩ ቀን የሰጣቸው የጎረቤቶቻችን  ልጆች በኪራይ ታክሲ ወደ ውድ የሆኑት ትምህርት ቤት ሲሄዱ ሲመለከቱ ወደፊት ምን አይነት ዜጋ ይወጣቸዋል ተብሎ ይጠበቃል። " ።

"ለነገሩ አነሳሁት እንጂ የዜግነት ጉዳይ ሲታሰብ እንደ አስፈራሪ ቅዠት ነው።የሃገር ፍቅር ፣ ለሃገሬ ምን ሠርቼ ልለፍ ብሎ ራስን መጠየቅ ፣ የዜግነት ትርጉምን ስታስበው ያስጨንቃል ። እንዲህ ግፍ በበዛበት ሃገር ራስን በሕይወት ከማቆየት አልፎ ፣ ቤተሰብን በበቂ አኗኗር ከመምራት ተርፎ፣ የዜግነት ግዴታን፣ የሠውነትን ተግባርና ኃላፊነት እንዴት ማሰብ  ይቻላል።"

"እስቲ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ ። ለሃገር ለወገን . . .  በቅርስነት የሚበቃ ተግባር ምንድነው ? የጥንቱ ኢትዮጵያዊ መሆን ? ዛሬ ያ ድሮ የምታውቁት የሕዝብ ፍቅር የለም ። እኔ እንጂ እኛ የሚለው ቀርቷል ። ሁሉም ሰው ባይባል ብዙው ራስ ወዳድ ነው ። በሌላው ሞት ራሱን የሚያድን ብልጥ ትውልድ ! የቀድሞው ኢትዮጵያዊ እምነት ፣ አስተሳሰብና ባሕል የሉም ። በወያኔና በጠላቶቻችን የተቀነባበረ ሤራ እኛ የሚለው ቃል ጠፍቷል። ዛሬ ችግር በሌሎች ላይ ሲደርስ ነገ በእኔ ነው ብሎ የሚነሳ ትውልድ እየጠፋ ነው"።

"ታስታውሱት እንደሆን ለአንድ አላማ ተሰልፈው ሕይወታቸውን መስዋዕት ያደረጉ ዘሮቻችንን አንረሳቸውም ። ለአመኑበት አላማ ረሳቸውን አሳለፉ ። አሁን የቀረው የእውነት ሰው አይዘነጋቸውም። እነሱ አለፉ ፣ አረፉ ። የተረፈ ግን ተከፋ፣ . . .  በብዙ መንገድ ተገፋ . . .  ያለፈ ትውልድና ቅሪቱን ፣ የአሁኑ ትውልድ አስተሳሰቡን በማነፃፀር ሞራላቸውን አቆሰሉ . . . እምነታቸውን ገደሉ . . .  ።  ያንን ትውልድ ለማጥፋት ሲሞከር ነው ነው ኢትዮጵያዊነትን መግደል የተጀመረው ። ለሃገር የሚያስበውን ትውልድ አላማውን ስንገታው፣ በሆነ በአልሆነ ሥጋውን ስንቦጭቀው፣

ስንሰድበውና ስናዋርደው የሚቀጥለው ትውልድ ራዕይ እንዳይኖረው ማድረጋችንን አሁንም ያልተረዱ ብዙ ናቸው። ዛሬ ለሃገር መስራት ከተፈለገ ያንን ዓይነት ትውልድ ለመፍጠር ነው መነሳት ያለብን ።ከራሱ አልፎ ለተበደለ ሕዝብ ሊጮኽ የሚችል"።

"ወደዚህ የመጣሁት ራሴን ለማዳን እንዳይመስላችሁ ። አይደለም ! እነዛን ሕፃናት ምን ላድርጋቸው ? ይኸኛውን መንገድ ሳልሞክረው በረሃብ ይለቁ ? መንገድ ላይ ይበተኑ ? ምን ልሁን ? ሌሊት እንባዬ አንሶላዬን እያራሰው እያደርኩ ፣ ቀን ልጆቼን ሳይ ሰቀቀን ሰውነቴን እየጨረሰው እንዴት ልኑር ? ራስን መቻል ራስን ከማጥፋት ከባድ ነው።"

" አትታዘቡኝ ከሃገሬ ወጥቼ በመሰደዴ አይደለም መሬት የሳምኩት ። ምንም የማያውቁትን ሕፃናት ነፍስ ያተረፍኩኝ መስሎኝ እንጂ " ብሎ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ ።

ሁለታችንም ይህንን አልጠበቀም ።በተለይ ጓደኛዬ ወንድሙ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ መገኘቱ በጣም አስደንግጦታል ። ሁለት ሦስት ጊዜ አዲስ አበባ ሄዶ ኑሮውን ተመክልቷል ። ይህንን ያህል ችግር በዚህ አምስት አመት ውስጥ ይደርስበታል ብሎ አላሰበም ። በመጨረሻ እያነባ እውነተኛውን የእንኳን ደህና መጣህ ሰላምታውን አቀረበ ። ወንድሜ አይዞህ እንረዳዳለን ብሎ አቅፎ ይስመው ጀመር ። እንባ በእንባ ሆኑ ። የወንድ ልጅ እንባ . . . አቅም ያጣ ሰው እንባ . . . የቤተሰብ ሃላፊነት ያለበት ሰው እንባ . . . ይህ ሁሉ ግፍ **በቃ** አያሰኝ ይሆን ?
ወንድማማቾቹ ሲላቀሱ ነው ቀስ ብዬ ወጥቼ የሎሬት ፀጋዬን ግጥም በቀስታ እየደገምኩ ጉዞዬን የጀመርኩት ፡-

ብቻውን ነው . . . ብቻውን ነው . . .
የእንባ ጨለማ ለብሶ ነው ፣
ወንድ ልጅ ወዙ እሚነጥበው ።

ዕጣውን ለብቻው ቆርሶ ፣
ብቻውን ሰቀቀን ጎርሶ ፣
ብቻውን ጨለማ ለብሶ ፣
ገበናውን ሳግ ሸፍኖ ፣
ክብሩን በሰቆቃ አፍኖ ፣
ሌሊት የማታ ማታ ነው ፣
ሕቅ እንቁን እሚነጥበው ፣
ኤሎሄውን እሚረግፈው . . .
ከዓይኑ ብሌን ጣር ተመጦ፣
ከአንጀቱ ሲቃ ተቆርጦ ፣
ደም አልሞ ፣ ፍም አምጦ ፣
ከአፅም - ወዙ እቶን ተፈልጦ ፣
እንደ ጠፈር ብራቅ እምብርት ፣
እንደ እሳተ ገሞራ ግት ፣
' ርቅ ነው ወንድ ልጅ እንባው
ደም ነው ፍም ነው የሚያነባው ፣
ንጥረ ሕዋስ ነው ሰቆቃው ፣
ረቂቅ ነው ምሥጢር ነው ጣሩ ፣ ብቻውን ነው የሚፈታው ፣
ብቻውን ነው የሚረታው ።

ግጥሙ እንዲህ እንዲህ እያለ ነበር የሚወርደው ። የዕንባ ምንጫና የዕንባ መፍሰሻ ጊዜ ሲጠቁም !

ይህ ታሪክ ልብ ወለድ እንዳይመስላችሁ ። በእኛ ላይ የሚደርሰው ግፍ በዝቶ በሰው ላይ የሚፈፀም ተግባር ባይመስለንም አካባቢያችንን ከቃኘን ዛሬ ሃገራችን ውስጥ በየቀኑ የምናየው ሰቆቃ ነው ።
ይህ ምክንያት አብዮት ለማስነሳት ይበቃ ይሆን ?
ስለ ተበደሉ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም !

በልጅግ አሊ ጀርመን ፍራንክፈርት
የካቲት 2011